# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር---230691

ቀን- ጥቅምት 08 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ረታ ቶሎሳ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

**አመልካች፡-** አቶ ካሳዬ አበባዉ ጠበቃ የሰላም ዜና - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሀይሉ ዳባ - ጠበቃ ኦልያድ ጋዲሳ - ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የፍርድ አፈጻጸምን የተመለከተ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት ተጠሪ የፍ/ባለመብት ሲሆኑ አመልካች ደግሞ የፍርድ ባለዕዳ ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 293706 ግንቦት 09 ቀን 2014 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 292993 ሰኔ 23 ቀን 2014 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ሲታይ፡- በዋናዉ ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል በነበረ ይዞታን የተመለከተ የሁከት ይወገድልኝ ጉዳይ በመ/ቁ 285294 መስከረም 04 ቀን 2013 ዓ.ም የተሰጠዉ ፍርድ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ 1ኛ ተከሳሽ/የአሁን አመልካች/ በይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተረጋግጦ ከተሰጣቸዉ 281 ካ/ሜ ዉጪ በመዉጣት የከሳሽን( የአሁን ተጠሪን) ይዞታ መያዛቸዉ ሕገ ወጥ እና የሁከት ተግባር ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁ.1149/3 መሰረት የሁከት ተግባሩ ሊወገድ ይገባል፤ 1ኛ ተከሳሽ(አመልካች) በይዞታ ተረጋግጦ

ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከተሰጣቸዉ ዉጪ ያለዉን ይዞታ ለከሳሽ(ለተጠሪ) እንዲለቁ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን ተጠሪም በዉሳኔዉ መሰረት እንዲፈጸምላቸዉ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ግንቦት 09 ቀን 2014 ዓ/ም ባቀረቡት የአፈጻጸም አቤቱታ መነሻነት የስር ፍ/ቤት ለፍ/ባለመብት/ለአሁን ተጠሪ/ 500 ካ/ሜ የሆነዉ ከፍ/ባለዕዳ እጅ/የአሁን አመልካች/ ሆነ ከባለቤታቸዉ ወ/ሮ ብርቱካን አጥናፉ እጅ በሀይል በማንሳት ለፍርድ ባለመብት አስረክበዉ ዉጤት እንዲልክ ለለሚ ኩራ ክ/ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት፤ ለለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 9 አስተዳደር ጽ/ቤት ዋና ስራ አስፈጻሚ እንዲሁም ለለሚ ኩራ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ ይጻፍ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታዉም ሊቀርብ የቻለዉ በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአፈጻጸም ችሎት የሰጠዉ ትእዛዝ በፍርድ ከተሰጠ ዉሳኔ ዉጪ በመዉጣት በፍርድ ባለ ዕዳ ከተያዘዉ ይዞታ 500 ካ/ሜ ተቀንሶ እንዲፈጸም ማለቱ አግባብ አይደለም፤ ፍ/ቤቱ ከስልጣኑ ዉጪ በመዉጣት የአስተዳደሩን ስራ በአፈጻጸም ሽፋን ይህን ቀንሰህ፤ ከእገሌ ቆርጠህ ስጥ ማለቱ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.96814፣152172 እና 101345 ላይ ከሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር የሚቃረን ነዉ፡፡ ክርክሩ የሁከት ክርክር ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ የመፋለም ክርክር ዉጤት እንዲኖረዉ በማድረግ መብት የሚያጣብብ ትዕዛዝ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ ትእዛዝ ከአመልካችም ሆነ ከባለቤታቸዉ 500 ካ/ሜ በኃይል በማንሳት ይሰጥ በማለት የሰጠዉ ትእዛዝ የሁከት ባህሪ ያለዉ ነዉ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ አሁን ተጠሪ ለክሳቸዉ መነሻ ያደረጉት ምክኒያት ጨርሶዉኑ የተቋረጠ ነዉ፡፡ የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ላይ የተመለከተዉን ንብረት የማፍራት መብት የሚጥስ ነዉ፡፡ በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤት ለመኖሪያ የተሰጠጣቸዉን ፍርድ ያላረፈበትን ይዞታ እንድለቁ ትዕዛዝ መስጠቱ የፍትህ መጓደልን ከማስከተሉም በላይ ከሥልጣኑ ዉጪ በመሄድ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ላይ የተመለከተዉን ንብረት የማፍራት መብትን  የሚጥስ ትዕዛዝ የሰጠ በመሆኑ እና በዋናዉ ጉዳይ ያልተሰጠን የአፈጻጸም ችሎቱ በራሱ ዉሳኔ በመስጠት ከይዞታቸዉ ላይ 500 ካ/ሜ ተቀንሶ እንዲያስረክቡ በማለት የተሰጠዉ የአፈጻጸም ትእዛዝ እንዲሻርላቸዉ የሚጠይቅ ነዉ፡፡

ይህም ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመመርመር በዋናዉ ጉዳይ በመ/ቁ.285294 ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ የአሁኑ አመልካች በካርታ ካላቸዉ 281 ካ/ሜ ዉጪ የያዙትን ያስረክቡ የሚል ሆኖ ሳለ የአፈጻጸም ችሎት 500 ካ/ሜ ያስረክቡ በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ ጥቅምት 01 ቀን 2015 ዓ.ም የተዘጋጀ 3 ገጽ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- የስር ፍ/ቤት በዋናዉ ዉሳኔ መሰረት ለአመልካች በካርታ ተረጋግጦ ከተሰጣቸዉ 281 ካ/ሜ ዉጪ በሕገ-ወጥ መንገድ አስፋፍተዉ የያዙትን የተጠሪን ይዞታ እንዲያስረክቡ ትዕዛዝ መስጠቱ ከዉሳኔ ዉጪ የተሰጠ የአፈጻጸም

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ ኣያገለግልም*

ትዕዛዝ ነዉ ሊባል አይችልም፡፡ አመልካች መብት ሳይኖራቸዉ አፈጻጸሙን ለማስተጓጎል ያቀረቡት ነዉ፡፡ በይዞታዉ ላይ አመልካችም ሆኑ ባለቤታቸዉ መብት እንደሌላቸዉ ቀደም ሲል በተደጋጋሚ ክርክር አቅርበዉ እስከ ሰበር ሰሚ ደርሶ ዉሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች ዕዉነታዉን በማዛባት በካርታ ተረጋግጦ ከያዘዉ 281/ካ/ሜ ይዞታ ላይ 500 ካ/ሜ ተቀናሽ ተደርጎ ለተጠሪ ይሰጥ በሚል በስር ፍ/ቤት የአፈጻጸም ትእዛዝ እንደ ተሰጠ አስመስሎ አቀረቡ እንጂ ፍ/ቤቱ በዋናዉ ዉሳኔ መሰረት በአርሶ አደር የይዞታ መብት ተጠቃሚነት መመሪያ መሰረት ተመላሽ ተደርጎ ለተጠሪ ከተሰጠዉ በግምት 500 ካ/ሜ ይዞታ ላይ አመልካች በካርታ ተረጋግጦ ከያዘዉ 281 ከ/ሜ ይዞታ ዉጪ በመዉጣት አስፋፍቶ የያዘዉን ይዞታ ያስረክብ የሚል ነዉ፡፡ የሥር አፈጻጸም ፍ/ቤቱ የሰጠዉ ትእዛዝ ከዉሳኔ ዉጪ በአፈጻጸም አዲስ ዉሳኔ እንደመስጠት የሚያስገምት አይደለም፡፡ አመልካች ለአፈጻጸሙ መነሻ በሆነዉ ዋናዉ ክርክር የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠበት የፍሬ ነገር ጭብጥ ላይ በድጋሚ እንደ አዲስ እያቀረበ ያለዉ ክርክር አግባብነት የሌለዉ በመሆኑ ዉድቅ እንዲደረግ የሚል ነዉ፡፡ አመልካችም ጥቅምት 14 ቀን 2015 ዓ.ም በተዘጋጀ 2 ገጽ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉ ነዉ፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘዉን አከራካሪዉን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረነዋል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ ምላሽ የሚያሻዉ ጭብጥ የስር ፍ/ቤት በዋናዉ ፍርድ በመ/ቁ.285294 ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ የአሁኑ አመልካች በካርታ ካላቸዉ 281 ካ/ሜ ዉጪ የያዙትን ያስረክቡ የሚል ሆኖ ሳለ የአፈጻጸም ችሎት 500 ካ/ሜ ያስረክቡ በማለት የሰጠዉ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠ ፍርድ እንደ ፍርዱ መፈጸም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች በተዘረጋው ስርአት አግባብ በመመራት ካልሆነ በስተቀር በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ሕጋዊ ባልሆነ እና ውሳኔውን ውጤት አልባ በሚያድርግ መልኩ ውድቅ ሊደረግ የሚችልበት ወይም ፍርድን በማስፈጸም ሰበብ ፍርድ ያላረፈበትን በአፈጻጸም አጣርቶ ፍርድ አሳርፎ የሚፈጸምበት አግባብ አይኖርም፡፡ ድንጋጌዎች በግልጽ የሚያስገነዝቡት የፍርድ አፈጻጸም ስርአት ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ ሌላ ሳይጨምር እሱኑ ወደ ተግባር ወይም ውጤት የሚለውጥበት ስርአት መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ያልተሰጠ ፍርድ በምንም መልኩ በአፈጻጸም ወቅት ፍርድ ተሰጥቶ የሚፈጸምበት የአፈጻጸም ስርዓት አይኖርም፡፡ ይህን አስመልክቶ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀድሞ በሰ/መ/ቁ 29344፤ 96814 እና በሌሎች መዛግብት ገዥ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ቅሬታ ለቀረበበት የአፈጻጸም ትዕዛዝ መነሻ የሆነዉ ፍርድ በስር ፍ/ቤት በመ/ቁ 285294 መስከረም 04 ቀን 2013 ዓ.ም የተሰጠዉ ፍርድ ሲሆን ተፈጻሚነት ያለዉ የዉሳኔዉ ክፍል የሚለዉ "… 1ኛ ተከሳሽ(የአሁኑ አመልካች) በይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተረጋግጦ ከተሰጣቸዉ 281 ካ.ሜትር ዉጪ በመዉጣት የከሳሽን(የአሁን ተጠሪን) ይዞታ መያዙ ሕገ-ወጥና የሁከት ተግባር ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149(3)

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መሰረት የሁከት ተግባርሩ ሊወገድ ይገባል ተብሏል፡፡ ስለሆነም 1ኛ ተከሳሽ(የአሁን አመልካች) በይዞታ ተረጋግጦ ከተሰጣቸዉ ዉጪ ያለዉን ይዞታ ለከሳሽ(ለተጠሪ) እንዲለቁ ተወስኗል፡፡" የሚለዉ ነዉ፡፡ ተጠሪ ይህን ዉሳኔ ለማስፈጸም ባቀረቡት የአፈጻጸም አቤቱታ የተሰጠዉና አሁን ቅሬታ የቀረበበት የአፈጻጸም ትዕዛዝ "ለፍርድ ባለመብት(ለአሁን ተጠሪ) 500 ካ.ሜ የሆነዉ ከፍርድ ባለዕዳ እጅ ሆነ ከባለቤታቸዉ ወ/ሮ ብርቱካን አጥናፍ እጅ በሀይል በማንሳት ለፍርድ ባለመብት አስረክበዉ ዉጤት እንዲልክ ለለሚ ኩራ ክ/ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት..." ትዕዛዝ ያስተላለፈበት ነዉ፡፡

በዋናዉ ፍርድ ተፈጻሚ በሆነዉ የዉሳኔ ክፍል ላይ አመልካች ለተጠሪ 500 ካ.ሜትር ያስረክብ ተብሎ የተሰጠ ዉሳኔ ባለመኖሩ ቢያንስ በዋናዉ ዉሳኔ ለአመልካች የተጠበቀላቸዉን መብት ማለትም በይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተረጋግጦ የተሰጣቸዉ 281 ካ.ሜ ሊነካ ስለማይገባ ጥንቀቄ ሊደረግ ይገባል፡፡ በርግጥ አመልካች በአጠቃላይ ይዘዉ የሚገኙት ከ781 ካ.ሜትር በላይ መሆኑ ከተረጋገጠ ለአመልካች በይዞታ ማረጋገጫ ተረጋግጦ የተሰጣቸዉ ይዞታ እስካልተነካ ድረስ አመልካችን ሊጠቅም የሚችል ትዕዛዝ ሊሆን ቢችልም ከፍርዱ ይዘት ዉጪ ለአመልካች በይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተረጋግጦ የተሰጣቸዉ 281 ካ.ሜ ግምት ዉስጥ ሳይገባ የይዞታ ስፋቱ ተገልጾ ዉሳኔ ያላረፈበትን 500 ካ.ሜትር ከአመልካች እጅ በሀይል በማንሳት ለተጠሪ በማስረከብ እንዲፈጸም የተሰጠዉ የአፈጻጸም ትዕዛዝ ዋናዉን ፍርድ ወይም ዉሳኔ ያላገናዘበ በመሆኑ ተገቢ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ የአፈጻጸም ትዕዛዝ በዋናዉ ጉዳይ ከተሰጠዉ ፍርድ ዉጪ በመሆኑ እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378 እና ተከታዮችን ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 293706 ግንቦት 09 ቀን 2014 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 292991 ሰኔ 23 ቀን 2014 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የስር ፍ/ቤት አመልካች በይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተረጋግጦ የተሰጣቸዉን 281 ካ.ሜትር ይዞታን ባላስጠበቀ መልኩ 500 ካ.ሜትር ለተጠሪ በማስረከብ እንዲፈጸም የሰጠዉ የአፈጻጸም ትዕዛዝ በዋናዉ ጉዳይ በመ/ቁ 285294 መስከረም 04 ቀን 2013 ዓ.ም ከተሰጠዉ ፍርድ ዉጪ በመሆኑ ተሽሯል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 285294 መስከረም 04 ቀን 2013 ዓ.ም በተሰጠዉ ፍርድ መሠረት ለአመልካች በይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጣቸዉን 281 ካ.ሜትር ይዞታ በማይነካ መልኩ ዉሳኔዉን ያስፈጽም ዘንድ ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በዳኞች እረፍት ጊዜ የተሰራ ነው፡፡

5. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም